# አማራንም ኢትዮጵያንም በአንድ ጊዜ ማዳን ይቻላል?

**Shenkut Ayele፣ እሑድ ነሐሴ 8 ቀን 2008 ዓም (Sun August 14, 2016)**

**(https://www.facebook.com/S.Ayele.Eth/posts/1102807873101597)**

---

ብዙ ወንድሞቼ ከሚጠይቁኝ ተደጋጋሚ ጥያቄ ዉስጥ አንዱ "አማራንም ኢትዮጵያንም በአንድ ጊዜ ማዳን ይቻላል? እኛ ስለ ኢትዮጵያ የምንጨነቀዉ ምን እዳ ስላለብን ነዉ?" የሚል ነዉ::

ይሄ ጥያቄ በአማራ ወጣቶች ዘንድ የመወያያ ርዕስ እየሆነ የመጣበት ዋናዉ ምክንያት ወያኔ አማራን ነጥሎ ለ25 አመታት የዘር ጥቃት እና ማጥፋት ስለፈጸመበት እና ከአማራ ህዝብ መራራ መከራ ዉስጥ በሚፈልቅ የታመቀ እልህ ነዉ:: እናም እንዲህ በቀላሉ የማይረባ ጥያቄ ተብሎ ሊታለፍ እንደማይገባዉ ብዙ ቁም ነገሮችን የያዘ ጥያቄ እንደሆነ አምናለሁ:: አማራ ህዝብ ላይ የወረደዉን መከራ ቀርቦ ያስተዋለ ማንም ሰዉ እንዳሰኘዉ የአማራ ወጣቶች የሚያነሱትን ጥያቄ ማጣጣል አይችልም::

ስለዚህ እንዲህ አይነቱን ጥያቄ በአንድ አረፍተ ነገር ጠቅልሎ መመለስ አይቻልም:: ግን የሚመስለኝን ሀሳብ እንደሚከተለዉ ማካፈል እሞክራለሁ::

የአንዳንድ ወንድሞቼ ንዴት እና እልህ ይገባኛል::በአማራ ህዝብ ላይ በወያኔ ዘመን የተሰራዉ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ እንዲሁም የዘር ማጥፋት ስራ ምንም አይነት አቋም ሊያስወስድ ይችላል:: አማራ ስለኢትዮጵያ ብዙ ለፍቶ ዉለታዉ መገደል ሆነ ስለዚህ ከእንግዲህ አማራ ኢትዮጵያን መርሳት አለበት ብሎ አንድ ሰዉ ቢከራከር መንደርደሪያ ሀሳብ ስላለዉ በስሜት የተነገረ ንግግር ሊባል አይችልም:: እዉነት ነዉ አማራ ተገፍቷል ብቻ ሳይሆን የዘር ማጥፋት ወንጀልም በስፋት ተሰርቶበታል::

ሆኖም ካሁን ብኋላ አማራ ስለ ቀሪዉ ኢትዮጵያ አይጨነቅ ማለት ግን የሚከተለዉን አጠቃላይ ሀገራዊ ቀዉስ እና አሁን ከተፈናቀለዉ እና ከተገደለዉ 5 ሚሊዮን አማራ በላይ በአስራ ሚሊዮን የሚከተል የዘር መጥፋት እንደሚከሰት አለማወቅ ነዉ::ይሄም ብቻ ሳይሆን በርካታ ሚሊዮን የሚሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያዉያኖች ወደ መተራረድ እና ብጥብጥ ዉስጥ ሲገቡ የሚከተለዉን መበታተን እንዲሁም ከምድረ ገጽ መደምሰስ አለማስተዋል ነዉ::

አማራ ብቻዉን በ85 ብሄረሰብ መሃከል ከዚያም ይባስ ብሎ ከትግረው፡ ከአፋሩ፡ ከኦሮሞዉ፡ ከደቡቡ ጋር የሚዋሰን መሬት ላይ ተቀምጦ እንዲሁም አማራ ክልል በሚባለዉ ምድር ላይ ሌሎች ትልልቅ ብሄረሰቦችን አቅፎ ይዞ ሳለ አማራን ብቻ ማዳን የሚለዉ አስተሳሰብ ብኋላ ላይ መዉጫ ወደሌለዉ ነገር ዉስጥ ይከታል:: የሌላዉ ብሄረሰብ ጉዳይ እና የኢትዮጵያም ጉዳይ በአጠቃላይ ካልተፈታ አማራዉ ብቻዉን እንዴት እፎይ ብሎ ሊቀመጥ ይችላል?

ኢትዮጵያን በአጠቃላይ ማዳን ካልተቻለ አማራዉን ብቻዉን ማዳን ይቻላል ወይ የሚለዉ ጥያቄ በጥልቀት ሊሰመርበት ይገባል:: በኦሮሚያ ከ15 ሚሊዮን በላይ አማሮች እንዳሉ ይገመታል::በአዲስ አበባ ብቻ ከሚኖረዉ አስራ ሚሊዮን ህዝብ (ኢ-መደበኛ ስታስቲክስ እንደሚጠቁመዉ) ዉስጥ ከ55 ፐርሰንት በላይ አማራ ነዉ:: በመላ ሀገሪቱ በደቡብ ብዙ ሚሊዮን የተበተነ አማራ አለ::ጋምቤላ እና ቤኒሻንጉል በሚሊዮን የሚቆጠር አማራ አለ:: አፋር በሚሊዮን የሚቆጠር አማራ ነዉ

ያለዉ::እና አማራ ስለመላዉ ኢትዮጵያ መጨነቅ የለበትም::መጨነቅ ያለበት ስለ አማራ ብቻ ነዉ የሚለዉ አስተሳሰብ ወደ መሬት ሲወርድ ብዙ ፈተናዎች ይገጥመዋል::

ስለዚህ ትክክለኛዉ አቋም የሚሆነዉ አማራንም ኢትዮጵያንም ማዳን የሚለዉ ነዉ ብዬ አስባለሁ:: አማራንም እንዲሁም ኢትዮጵያንም ማዳን የሚቻለዉም ዲሞክራሲያዊት እና ሁሉም ኢትዮጵያዉያን የሚስማሙበት ስርዓት መገንባት ሲቻል ነዉ::

አማራን ብቻዉን ነጥሎ ማዳን ብሎ ማሰብ ግን ኋላ ላይ የሚከሰተዉን ዉስብስብ ነገር አሁን ለጊዜዉ እንዘንጋዉ እና እማሸነፍ ላይ እናተኩር ማለት ነዉ:: ለማሸነፍ ለማሸነፍ እማ ቢሆን ኖሮ ወያኔ አሸንፎ ስልጣን ይዞ ነበር::ግን ሁሉንም ኢትዮጵያ ሰላም እና እረፍት የሚሰጥ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት ስላልቻለ የኢትዮጵያንም ህዝብ የትግራይንም ህዝብ ታላቅ መከራ እና ጭንቅ ዉስጥ ጥሏቸዋል::ማሸነፍ በራሱ እንደ ግብ መወሰድ የለበትም::እንደ ግብ መወሰድ ያለበት የምትፈጠረዉ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ብሎም ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚስማማባት እና የሚረካባት የበለጸገች ሀገር መገንባት መቻሉ ነዉ::

የአማራ ህዝብ ወያኔ መጥቶ ከሁሉም ኢትዮጵያዉያን ጋር እንዲቆራረጥ የፖለቲካ ፕሮፖጋንዳ እና ደባ ሰራበት እንጅ በሌሎች ኢትዮጵያዉያን ወንድሞቹ ዘንድ የቅቡልነት ችግር የለበትም::አማራዉም ሌሎች ኢትዮጵያዉያን ወንድሞቹን የመቀበል ችግር የለበትም::በርካታ የስነልቦና: የባህል:የዘር: የመልክ ዓምድር: የታሪክ እና የምጣኔሃብት ዉርርስ እንዲሁም የወደፊት ታላቅ የጋራ ትልቅ ሀገራዊ እምቅ ራዕይ እና ትስስር ያለዉ ህዝብ ነዉ:: ስለዚህ አማራንም ኢትዮጵያንም ማዳን ላይ ማተኮሩ የበለጠ አዋጭ ነዉ ብዬ አስባለሁ::ደግሞም ይቻላል::

ለዚህ ሁሉ አዎንታዊ ሁኔታ እንቅፋት የሆነበት አንድ ሰይጣናዊ ሀይል ወያኔ ብቻ ነዉ::ወያኔ ሲነቀል ከሁሉም ኢትዮጵያዉያን ወንድሞቹ ጋር ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መፍጠር እና በመከባበር መኖር ይቻላል የሚል አመለካከት አለኝ:: እንኳን ኢትዮጵያን የምታክል ትንሽ አገር ትቅር እና አሜሪካን እና ሩሲያን እንዲሁም ቻይናን የሚያካክሉ ታላላቅ የህዝብ ቁጥር: የመልክ ዓምድር ስፋት እና የማህበረሰብ ልዩነት ያለባቸዉ ሀገራት የሀገሪቱ ዜጎች ተስማምተዉ የሚኖሩበትን ሰፊ እና ዲሞክራሲያዊት ስርዓት በሰፊ መሰረት ላይ መዘርጋት በመቻላቸዉ እንዲሁም እየተወያዩ እና እየተከራከሩ አካታች ስርዓትን እየገነቡ በመምጣታቸዉ ሀይል እና ጉልበት ያላቸዉ ሀገራት እንዲሁም ተሰሚነት ያላቸዉ ህዝቦች መሆን ችለዋል::በኢትዮጵያዉያን መሃከልም ያሉ የማህበረሰባዊ ልዩነቶች መፈታት ያለባቸዉ በዚህ መልክ ነዉ:: ከሰለጠነዉ አለም በሚወሰድ ሞዴል አሰራር ማለት ነዉ::ከዚያ በፊት ግን ወያኔ መነቀል አለበት::

ስለዚህ የአማራ ሰዉ ሁሉ እንደ መሰለዉ አሁን ትግሉን በሁለት መልክ ማጧጧፍ ላይ ማተኮር አለበት እንጅ ሌላዉ ነገር ሊያስጨንቀዉ እና እርስ በርሱ አንዱ አንዱን በመንቀፍ መጨቃጨቅ የለበትም የሚል ግንዛቤ አለኝ:: አንድም በአማራነት በብሄሩ በመደራጀት ወያኔን መታገል::ወይም ደግሞ ከሌሎች እዉነተኛ ኢትዮጵያዉያን እና አማራን ከማይጠሉ ኢትዮጵያዉያን ጋር በመሆን በኢትዮጵያዊነት በመደራጀት ወያኔን መታገል::ሁለቱም አካሄዶች ግባቸዉ አንድ ይሆናል ብዬ አስባለሁ::ይሄዉም ወያኔን በመንቀል ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መፍጠር የሚለዉ ግብ ይሳካል ብዬ አስባለሁ::